ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረመዳን 21/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስትር አፕሪል 22/4/2022 ግ.

# የመጨረሻዎቹ አስር ቀናትና የዘመናችን ቅድሚያዎች ደንብ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ سَابِقُوا إِلَى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا كَعَرْضِ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ أُعِدَّتْ لِلَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ }

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡
ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነችም ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡ ለእነዚያ በአላህና በመልክተኞቹ ላመኑት ተዘጋጅታለች፡፡)

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል
አላህ (ሱ.ወ.) ለባሮቹ ከለገሳቸው ችሮታዎች አንዱ በተከበረው የረመዳን ወር ያሉትን የመጨረሻ አስር ሌሊቶች የመልካም ስራ መጨመሪያና ለደግ ነገሮች መሽቀዳደሚያ ጊዜ ማድረጉ ነው፡፡ የወሩ መጨረሻ በሚቃረብበት ወቅት መንፈስ የበለጠ ለመልካም ስራ ትነሳሳለች፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በእነዚህ ሌሊቶች ያለውን መልካም

እድል በሚገባ ይጠቀሙበት እንደነበር (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ በማለት ገልጸውታል፡ ‹‹የአላህ መልክተኛ በረመዳን የመጨረሻዎቹ አሰስር ቀናት ከሌላው ጊዜ በበለጠ ለመልካም ስራ ጥረት ያደርጉ ነበር››፡፡ እንዲሁም በሌላ አጋጣሚ እንድህ ብለዋል፡ ‹‹የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በሚጀምሩበት ወቅት የአላህ ምልክተኛ ሌሊቱን ያለአንቅልፍ ያሰልፉ፣ ቤተሰቦቻቸውን ያነቃቁና ባጭር ይታጠቁ ነበር››፡፡

የረመዳንን የመጨረሻ አስር ሌሊቶች በስግደት፣ ቁርኣንን በመንበብ፣ አላህን በማወደስ፣ ከአላህ ምህረትን በመጠየቅ፣ ምጽዋት በመስጠትና በሌሎችም መልካም ስራዎች ነቅቶ ማሳለፍ የነበዩን ፈለግ በሚገባ መከተል ማለት ይሆናል፡፡ ይህም የጻዲቃንና የፈሪሃ ኣላህ አገልጋዮች የዘወትር ተግባር እንድሁም እሱ የጀነት ሰዎች ባሕርይ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{ تَتَجَافَى جُنُوبُهُمْ عَنِ ٱلْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنفِقُونَ * فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَا أُخْفِيَ لَهُمْ مِنْ قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَاءً بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ}

(ጌታቸውን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ጸጋ) ይለገሳሉ፡፡ ይሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም፡፡

እንድሁም አላህ (ዐ.ወ.) ፈሪሃ አላህ የሆኑ ባሮቹን ገጽታ እንድህ በማለት ገልጹዋል፡

{إِنَّ ٱلْمُتَّقِينَ فِي جَنَّاتٍ وَعُيُونٍ *آخِذِينَ مَا آتَاهُمْ رَبُّهُمْ إِنَّهُمْ كَانُوا قَبْلَ ذَلِكَ مُحْسِنِينَ * كَانُوا قَلِيلًا من اللَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ * وَبِالْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ}

(አላህን ፈሪዎቹ በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው፡፡ ያንን ጌታቸው የሰጣቸውን ተቀባዮች ኾነው፤ (በገነት ውስጥ ይኾናሉ)፡፡

እነርሱ ከዚህ በፊት መልካም ሰሪዎች ነበሩና፡፡ ከሌሊቱ ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበሩ፡፡ በሌሊቱ መጨረሻዎችም እነርሱ ምሕረትን ይለምናሉ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በሌሊት አላህን መገዛትን አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ እሱ ከናንተ በፊት የነበሩ ጻዲቃን የዘወትር ተግባር፣ ወደአለላህ መቃረቢያ፣ የኃጢያት መከለከያ፣ የመጥፎ ተግባር ማስተሰረያና ከአካል በሽታን ማስወገጃ ነውና)፡፡

የረመዳን ወር ከእሳት ነፃ መውጫ ወር ነው፣ ከሌሊቶቹ አንዱም ሌሊት ለአላህ በርካታ ባሮቹ ከእሳት ነፃ የሚወጡበት ቢሆኑ እንጂ አያልፍም ስንል ይህ ተስፋ በነዚህ በመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በጣም ሰፊ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ እንድሁም አላህ (ዐ.ወ.) በሌሊት ምህረት ለሚጠይቁት ምህረትን ይለግሳል ስንል ይህ የአላህ እዝነትና ምህረት በነዚህ ቀናት የበለጠ ተስፋ ይደረግበታል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ቀናት አላህ (ዐ.ወ.) ከሌሎች ሌሊቶች በበለጠ ያከበራትን የቀድርን ሌሊት ያካትታሉና ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እድህ ይላሉ፡ ( የቀድርን ሌሊት ከረመዳን በመጨረሻዎቹ አስር ቀናት አፈላልጓት)፡፡

ይህች የተባረከች ሌሊት በሷ አላህ (ዐ.ወ.) ደረጃው በጣም ታላቅ የሆነን መጽሐፍ ደረጃው በጣም ታላቅ በሆነ መላእክ አመአካነት ደረጃው በጣም ታላቅ ለሆነ ነብይና ደረጃው ታላቅ ለሆነ ህዝብ ያወረደባት የሌሊቶች እንቁ ሌሊ ናት፡፡ በዚህች ሌሊት የአላህ ምህረት፣ እዝነቶችና በረከቶች የሚወርድባት መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{إِنَّا أَنْزَلْنَاهُ فِي لَيْلَةِ الْقَدْرِ * وَمَا أَدْرَاكَ مَا لَيْلَةُ الْقَدْرِ * لَيْلَةُ الْقَدْرِ خَيْرٌ مِّنْ أَلْفِ شَهْرٍ * تَنَزَّلُ الْمَلاَئِكَةُ وَالرُّوحُ فِيهَا بِإِذْنِ رَبِّهِمْ مِنْ كُلِّ أَمْرٍ * سَلاَمٌ هِيَ حَتَّى مَطْلَعِ الْفَجْرِ}

(እኛ (ቁርኣኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው፡፡ መወሰኛይቱም ሌሊተ ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺሕ ወር

በላጭ ናት፡፡ በርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ፡፡ እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የቀድርን ሌሊት በእምነትና ምንዳን በመፈለግ ነቅቶ ያሳላፈ ሰው ከዚያ በፊት የነበረው ወንጀሉ ይሰረዝለታል)፡

እዚህ ላይ ልናረጋግጠው የምንፈልገው ነገር ቢኖር ልቦችን ማላመድና ራስን ወደመልካም ተግባር መመለስ መልካም ስራዎች ተቀባነት ማግኘታቸውን የሚጠቁሙ መሆናቸውን፣ በአንፃሩም አለመግባባትና መጋጨት መልካም ምነዳዎችን የማጣት መንገድ መሆናቸውን ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በነዚህ በተከበሩት ሌሊቶች፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እኔ ስለቀድር ሌሊት ልነግራቹሁ ወጣሁ፡፡ በዚያን ወቅት እገሌና እገሌ ተጨቃጨቁና ተነሳች፡፡ ይህም ለናንተ  ደግ ነገር እንዲሆንላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ)፡፡ በሌላ ሐዲስ ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (በሱም ከአንድ ሺህ ሌሊት የምትበልጥ ሌሊት አለች፡፡ በሷ ደግን ነገር ያላገኘ ሰው ታለቅን ነገር አጥቷል)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

በነዚህ ቀናትና በተባረኩት ሌሊቶቹዋ የኢባዳ መስኮች በርካታና የተለያዩ ናቸው ስንል ልባም የሆነ ሰው ተቀዳሚነት ያለቸውን ተግባራት በተራ ማስቀመጥና ጥቅሙ ሰፊ የሆነውን ተግባር ጥቅሙ አነስተኛና ውስን ከሆነው  ተግባር አስቀድሞ ማከናውን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በነዚህ

ቀናት የፊጥርን ዘካ ማዘጋጀቱን ቀድሞ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ እንድሁም ለድሃዎች፣ ምስኪኖችና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሙስሊሙ ህብረተሰብ አባላት ኢዱ ሳደርስባቸው ጉዳያቸውን ለማውጣት እንዲያግዛቸው ከኢድ በፊት ቀድሞ ለመስጠት መሞከርም ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እነሱን በዚህ ቀን ከመጠየቅ እድኗቸው)፡፡ በፊጥር ዘካ የጥራጥሬዉን ዋጋ መስጠት ይቻላል፡፡ በአለንበት ዘመንና በማህበረሰባችን ሁኔታ ጉዳይን ለማውጣት በበለጠ የሚያግዘውና ከእስልምና ደንብ አላማዎች ጋር ተጣጥሞ የድሃዎችን ጥቅም የሚያሟላው ጥሬ ገንዘብን መስጠት ነው፡፡

በተደጋጋሚ ሀጅንና ዑምራን ከመፈጸም ይልቅ ደሃዎችንና ምስኪኖችን ማብላትና ማጠጣት የሚበልጥ መሆኑ ከእስልመና ደንብ አላማዎች ዋነኛው ነው፡፡ የመጀመሪያ ምልካም ስራ በአካል ወይም በከፊል ማህበረሰብ መፈጸም ያለበት ግዴታ ሲሆን የኋለኛው (ተደጋጋሚ ሀጅ) በፈቃድ የሚፈጸም መልካም ስራ ነው፡፡ በአካል ወይም በከፊል ማህበረሰቡ አማካይንት መፈጸም ያለበት ተግባር ከሁሉም በፈቃድ ከሚደረሱ መልካም ስራዎች ሁሉ ተቀዳሚ መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ ከዚያም አልፎ የጭንቀኞችን ጭንቅ ማስወገድ ያለው ምንዳ እጅጉን ታላቅ ምንዳ ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከሰዎች እጅግ አላህ ዘንድ ተወዳጁ ለሰዎች ያለው ጥቅም የበለጠ የሆነ ሰው ነው፡፡ አላህ ዘንድ አጅግ ተወዳጁ መልካም ስራም በሙስሊም ልብ ደስታን ማስገባት፣ ወይም ከሱ ጭንቅን ማስወገድ፣ ወይም የሱን ጉዳይ ማውጣት፣ ወይም ከሱ ረሃብን ማስወገድ ነው)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ከዚህች አለም ጭንቀቶች አንድን ጭንቀት ከሙስሊም ላይ ያቃለለ ሰው አላህ (አ.ወ.) ከቂያማ እለት ጭንቀቶች አንድን ጭንቅ ያቃልለታል)፡፡

ጌታችን ሆይ ጾማችንና ስግደታችንን ተቀበል፡፡ ሀገራችንን ግብጽንና ሌሎችንም የአለም ሀገራት ከመትፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሚን፡፡